# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

በዚህ ዕለት ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ስለ ጻድቃንና ስለ ኃጥአን ፍርድ ይታሰባል። ይሰበካል። (ይህ ዕለት በጊዜዎች መሳሳብ የሚቀርበትም ዓመት አለ።)

## የዕለቱ ምስባክ

ለካህናቲሃ አጸግቦሙ እክለ
ወለካህናቲሃ አለብሶሙ ሕይወተ
ወጻድቃኒሃ ትፍሥሕተ ይትፌሥሑ

ድሆችንም እንጀራ አጠግባለሁ
ካህናቶችዋንም ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ
ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል።

መዝ ፻፴፩፥፲፮-፲፯

## የዕለቱ ትምህርት

ወንጌል፦ ሉቃስ ፲፪፥፴፪-፵፩
ቅዳሴ፦ የቅዱስ አትናቴዎስ

## ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁ የበራ ይሁን

(ሉቃስ ፲፪፥፴፭)

በቅዳሴ ጊዜ በአንደኛው ዲያቆን የተነበበው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና የክርስቶስም ትንሣኤም የትንሣኤ ቅዱሳን መሠረት መሆኑን የክርስቶስ ትንሣኤ መጽደቂያችን፣ መክበሪያችን መሆኑን የዚህች ዓለም ሕይወት ከንቱ መሆኑን፣ ለምድራዊ ሕይወት ብሎ ክርስቶስን ያመነ አለመኖሩን በማስገንዘብ በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን ብሎ ይናገራል። በማስከተልም ክርስቶስ በትንሣኤው በኩረ ምእመናን መሆኑን እየሰበከ እኛም ተነስተን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደምንወርስ የሚሞተው የማይሞተውን፣ የሚፈርሰው የማይፈርሰውን፣ የሚያልፈው የማያልፈውን እንደሚወርስ ይናገራል። ምስባኩም በመንግሥተ እግዚአብሔር በጽድቀ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ጻድቀን ከመንፈሳዊ ረሃብ ድነን የምንኖር መሆኑን ያስገነዝባል። በመልእክተ ጴጥሮስም በመንግሥተ እግዚአብሔር

| የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ |
|---|
| ሥርዐ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ<br>(ሰንበትን) መንግሥተ ሰማያትን ለሰው ዕረፍት ፈጠረ። |

**በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች**

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፲፪-፴፫ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፪ኛ ጴጥ ፫፥፲ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፥፳፰ እስከ ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

ክፉ ሰዎች ለፍርድ እንደሚጠበቁ ተጽፎአል። የተነበበልንም ወንጌል እግዚአብሔር መንግሥትን ሊሰጠን መዘጋጀቱን (ሉቃ ፲፪፥፴፪) እኛም እንደ ሙሽራ ሆኖ የሚመጣውን ጌታ ለመቀበል (በማቴ ፳፭) እንደተጠቀሱት ደናግል ወገባችን የታጠቀ መብራታችን የበራ ሆኖ እንዲገኝ ይመክረናል።

በምሳሌም ባለቤቱ በሩን ቢያንኳኳ የቤቱን በር ቶሎ እንደሚከፍቱት ባርያዎች እንድንተጋ ተግተን ብንጠብቀው በሕይወት ማዕድ በምስሐ ደብረ ጽዮን እንደሚያስቀምጠን እንዲሁም ሌባ መቼ መጥቶ እንደሚሰርቅ ባለንብረት ቢያውቅ ተግቶ ንብረቱን እንደሚጠብቅ ነገር ግን ሌባ ባልታሰበበት ቀን መጥቶ እንደሚሰርቅ እንዲሁ ጌታም ድንገት ባልታሰበ ሰዓትና ዕለት እንደሚመጣ አስተምሮናል።

**አንባቢ ሆይ፥**
ጌታህ ድንገት ይመጣል። ዋጋውም ከእርሱ ነው። ሌሊቱን ሕይወትህን ጠብቅ፤ በንስሐም ሊቀበልህ ወደ አንተ መጥቶ ሲያንኳኳ በሩን ክፈትለት ሰነፍ ባሪያ አትሁን። ጌታህ ከውጭ እንዳይቆም መብራትህንም አብራ ማለትም በሃይማኖት በበጎ ሥራ በንስሐ ሕይወት ተከናወን፤ ጌታህ ድንገት ይመጣል። በመቃብርም ላሉት ድምጹን ያሰማል፤ ሙታንም ይነሳሉ። ጻድቃን ክብሩን መንግሥቱን፣ ኃጥአን መዓቱን ቁጣውን ይወርሳሉ። የተራቡ ይጠግባሉ፤ የተጠሙ ይረካሉ። አገልጋዮችም ጽድቅን ይለብሳሉ፤ ለኃጥአን ይመጣባቸዋል ለጻድቃን ይመጣላቸዋል። ለአንተስ ይመጣልህ ይሆን ወይስ ይመጣብህ?

ወሰብሃት ለእግዚአብሔር አሜን።

ከመምህር ልዑል ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM